# የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)

## Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

መጋቢት 7 ቀን 2001 ዓ.ም.

### የድሬዳዋ የምድር ባቡር ሰራተኞች እንቅሰቃሴን ኢሕአፓ ይደግፋል

ከሶስት ወር ላለነሰ ጊዜ አለደሞዝ መሰቃየት፣ የቤት ኪራይ መክፈል አለመቻል፣ የልጆችና የቤተሰብ የምግብ ችግር መሸከም፣ ኮረንቲና ውሀ አገልግሎቶች መቋረጥ፣ አንዱ የተበደለ ሠራተኛ እንዳለው ባለስልጣኖቹ ትልቅ ሆዳቸውን ሲሞሉ ላባደሩ ትንሽ ሆዱን ሊሞላ ወይም በገሚስ ረሀቡን ጋብ ሊያደርግም የሚችልበት ሁኔታ በመዘጋቱ የምድር ባቡር ሠራተኞች በሰሞኑ ተቃውሞአቸውን አሰምተዋል:: ኢሕአፓ የምድር ባቡር ሠራተኞች ያካሄዱትን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ደግፎ ሌሎች ማህበራትም ድጋፍ ሰጥተው ከጎናቸው መቆማቸውን ያደንቃል፣ ያበረታታል::

ወደ ኢትዮጵያ መግባት ያለባቸው ቆሳቁሶች በጅቡቲ ወደብ ተጨናንቀው እያሉ፣ የምድር ባቡሩን ቫጎኖች ለሌላ ተጠቃሚ ሰጥተው የምድር ባቡሩን አቅም ያዳከሙና የአስተዳደር ችሎታ ድክመት ያሳዩ የወያኔ ሹመኞች እነ አቶ አየለ ወልደየስና ሌሎችም ከቦታቸው እንዲነሱ የጠየቁት ሠራተኞች ለባልሥጣን አቤት ከማለት ለአምላካችን ፀልየ  መፍትሄ መጠበቁ ይበልጥ ያዋጣናል ሲሉ ምሬታቸውን ገልጠዋል:: የወያኔ አገዛዝ በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ላባደሮችን እየበደለና ለከፋ ብዝበዛ እያጋለጠ መሆኑ የሚታወቅ ነው:: የሰፈነው የኤኮኖሚ ቀውስ፣ የምግብ ዋጋ በመቶ እጅ መናሩ፣ ሠራተኛው በቂ ክፍያ አለማግኘቱ፣ በወያኔ ሹመኞቾ መበደሉ፣ በጊዜ ደሞዙን አለመከፈሉ ለባሰ ችግር መጋለጡ፣ የሥራ ሁኔታው በጠቅላላው መበላሸቱ ሊደበቅ የሚችል አይደለም:: ኤኮኖሚው አድጓል፣ አገር እየለማች ነው፣...ወዘተ በሚል ነጋ ጠባ ዓይኑን በጨው አጥቦ እየዋሸ ያለው የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያ ላባደሮችን ፅኑ ትግል ገና ያላየ በመሆኑ ቢዝናናም እየመጣ ያለው የተባባረ ተቃውሞ ከሥልጣኑ የሚያናጋው ሊሆን እንደሚችል ግን መገመቱና መፍራቱ የሚጠበቅ ነው:: የምድር ባቡር ሰራተኞች ቁልፍ ቦታን የያዙ ለሀገሪቷ ኤኮኖሚም መሰረት የሆኑ ናቸውና ተቃውሟቸውና አድማቸው አንደምታው በቀላሉ የሚታይ አይደለም:: ኢሕአፓ የጀመሩትን መሰረታዊ መብት የማስከበር ትግል እንዲገፉበት እየጠራ ሌሎችም ቁልፍ ቦታ የያዙ ሠራተኞችም በተመሳሳይ እንቅስቃሴ እንዲያጅቧቸው ጥሪ ያደርጋል:: የደሞዝ አለመከፈል፣ የኑሮ ውድነት÷ ረሀብና መከራን ማስወገድ የሚቻለው በተቃውሞ፣ በስራ ማቆም አድማና አገዛዙ  በማንበርከክ ብቻ ነው::

ኢሕአፓ ባለ 11 ነጥቡን የምድር ባቡር ሠራተኞች የአቅዋም ውሳኔ ይደግፋል:: የተቃውሞ ትግላቸው ፍትሀዊ ነውና ከጎናቸው ይቆማል:: መብት የሚረጋገጠው በትግል ነውና ሌሎችም ሠራተኞች የምድር ባቡር ሠራተኞችን ደግፈው ዓርዓያነታቸውንም በመቀበል ሀገር አቀፍ የላባደሩ የተቃውሞ የጋራ ትግል እንዲፋፋም ኢሕአፓ ጥሪውን ያስተላልፋል:: የሠራተኛው ማህበራትንም ከወያኔ ቁጥጥር ነፃ ማድረግ ወሳኝ መሆኑንም ጫና ይሰጣል::

የላባደሮች ፍትሀዊ ትግል ድልን ይቀዳጃል!!

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France